# የድርጊት መርሐ ግብር - ፖሊሲ

BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ግብአቶች ፡-** ACA, JEB-RA, JEB-RB, JEB-EA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** የአካዴሚ ዋና ኃላፊ

## ወደ ቅድመምዋዕለ ህጻናት/Prekindergarten፣ ምዋዕለ ህጻናት/Kindergarten፣ እና አንደኛ ክፍል/First Grade

A. **ዓላማ**

ቀደም ብሎ በጊዜ የተጀመረ የልጆች ትምህርት ለወደፊት ቀጣይ ትምህርታቸው ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ጥልቅና ጠንካራ መሠረት ይሰጣል። ለረዥም-ጊዜ የትምህርት ተሞክሮ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደመሆናቸው መጠን፣ ወደ ቅድመሙዋእለ ህፃናት፣ ሙአለ ህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል የሚገቡ ተማሪዎች ለመማር ዝግጁ መሆናቸውን እና ስኬታማ እንደሚሆኑ ለማረጋገጥ የሚቻለው ሁሉ ጥረት ይደረጋል። ቀደም-በጊዜ ስለሚጀመር የልጆች ትምህርት የረዥሙን-ጊዜ ውጤት ከእያንዳንዱ ተማሪ ልዩ ፍላጎቶች ጋር አሁን ባለው ግንዛቤ በሚዛናዊነት ለመገንዘብ ጥንቃቄ የተሞላበት ምልከታ ያስፈልገዋል። በስቴት ደንብ-ድንጋጌ መሠረት፣ የትምህርት ቦርድ ባለው አመለካከት በአጠቃላይ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መግባት-ትምህርት መጀመር ያለባቸው ለረዥሙ-ስኬታማነት እንዲያመቻቸው በምርምር በተረጋገጠ እድሜ ቢሆን የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ነገር ግን፣ ስለ ተማሪዎች ቀደም ብለው-በጊዜ ትምህርት ስለመጀመር ይህ ፖሊሲ እና የስቴት ደንብ የግለሰብ ፍላጎት-ሁኔታን ግምት መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል።

B. **ጉዳዮች**

ቀደም ብሎ-በጊዜ ወደ ቅድመምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል የመግባት ውሳኔ፣ ሁሉንም እውነታዎች ግምት የማስገባት ጥንቃቄ የተሞላበት አሠራርን ይጠይቃል። አካደሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ዝግጁነት፣ እንዲሁም የተማሪው(ዋ) አካላዊ የእድገት ሁኔታ እና ደህንነት፣ እና ተቋማዊ እውነታዎች ጭምር መመዘን ይኖርባቸዋል። ቀደም-በጊዜ ወደ ቅድመምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል በመግባት ረገድ ጠቃሚ ውሳኔ የመስጠት ሁኔታ የሚወሰነው፣ ስለተማሪው(ዋ) ዝግጁነት እና በርካታ እውነታዎችን በማስተዋል እና ውሳኔው የሚያስከትለውን ውጤት ጭምር ለማመዛዘን አስተማማኝ በሆነ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ላይ የተሞረኮዘ መሆን አለበት።

C. **አቋም**

በትምህርት ቦርድ ታሳቢ የሚደረገው በስቴት ደንብ-መሠረት ተማሪዎች ወደ ቅድመምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል እንደሚገቡ ነው። ትምህርት ቤት የመግባት ሁኔታ በተወደለዱበት ቀን ምክንያት ለጥቂት ያመለጣቸው ተማሪዎች ወደ ቅድመምዋእለ ህፃናት፣ ምዋእለ ህጻናት፣ እና አንደኛ ክፍል ቀደም-በጊዜ መግባት የሚያስችላቸው ፍላጎትና አቅም ያዳበሩ መሆኑን የትምህርት ቦርድ ይገነዘባል።

1. በስቴት ደንብ መሠረት የገቢ-ብቃት ላላቸው ቤተሰቦች የቅድመምዋእለ ህፃናት ተደራሽነት እድል አላቸው። ወደ ቅድመሙዋእለ ህጻናት ቀደም-በጊዜ ለመግባት የሚፈልጉ በአስተዳደጋቸው የዝግጁነታቸው ደረጃ፣ ት/ቤት ለመግባት እንደሚችሉ አስተማማኝ እንደሚሆን በማሳየት እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል።

2. ወደ ሙዓለ ህፃናት ቀደም-በጊዜ ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎች ቀድሞ ለመግባት የመቻላቸውን-ብቃት ማሳየት/demonstrate አለባቸው።

3. ወደ አንደኛ ክፍል ቀደም-በጊዜ ለመግባት የሚፈልጉ ተማሪዎች ለመግባት የመቻላቸውን-ብቃት ማሳየት/demonstrate አለባቸው።

4. ቀደም-ስለመግባት የሚደረጉ ውሳኔዎች የግለሰብ ነባራዊ እውነታዎችን ወይም በይሆናል የሚታሰቡ የግል ባህርያትን የማግለል ምክንያት ሳይደረግ በ Board Policy ACA፣ ድንጋጌ መሠረት መፈጸም አለባቸው Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency። እንደ ተቋማዊ አቅም የመሣሰሉ እውነታዎችንም ግምት መሰጠት አለባቸው።

**D. የአተገባበር ስልቶች**

1. ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ሱፐር ኢንተንደንቱ ደንቦችንና-መመሪያዎችን ያዛጋጅል፤ ይኼውም በምልመላ ውሳኔዎች ምክንያት የሚነሱ ቅሬታዎችን ይግባኝ የማቅረብ ሥርዓትን ጭምር የተወለዱበት ቀን በስቴት ከተደነገገው የትምህርት ቤት መግቢያ ቀን ስድስት-ሣምንት በኋላ የሆኑትን ስለመመልመል ሂደት ይጨምራል።

2. በትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች ላይ በመመስረት የተዘጋጁ ደንቦች በጠቅላላ የመረጃ ሠነድ ተደርገው ወደ ቦርድ መላክ አለባቸው።

**E. ግምገማ እና ሪፖርት**

ይህ ፖሊሲ በቦርድ የማሻሻያ መመሪያ መሰረት ይገመገማል።

**ተዛማጅ ምንጮች፦** Code of Maryland Regulation 13A.08.01.02

የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፦ የውሳኔ ቁ. 543-83፣ ጁን 14/1983፣ በውሳኔ ቁጥር --እንደገና ማሻሻያ ተደርጎበታል 333-86፣ ጁን 12፣ 1986፤ እና ውሳኔ ቁ. 458-86፣ ኦገስት 12፣ 1986፣ የፀደቀው በውሳኔ ቁ. 517-86፣ ሴፕቴምበር 22፣ 1986፤ ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ ቁ. 211-04፣ ኤፕሪል 15/2004፣ በውሳኔ ቁጥር 145-06፣ ማርች 14/2006በሥራ ላይ ዋለ፣ በውሣኔ ቁጥር --ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። 319-17፣ ጁን 26/2017።